# ተግተን እንለምን

ዮዲትና ግራኝ ፣ የበሸሻዎቹ
መርዝ ወልደው ያለፉ ፣ የትላንትኖቹ
አፅራረ ኦርቶዶክስ ፣ የሌሎች አቢቹ
ከኒህ አላፊዎች ፣ በተገኘው ፍሬ
ፈተናዋ በዛ ፣ ስቃዩዋ የሐገሬ
መዓቱን ያዘንባል ፣ አርዮስ አጅሬ ።

በሸንገላ ምላስ ፣ የሚቀባጥረው
ሆድ አምላኩ አጋሰስ ፣ ለባዕድ ያደረው
ትንሹን ትልቁን ፣ ሐገር ያስመረረው
እርኩሳን መናፍስት ፣ የሚሽከረከረው
ከጅማው በሻሻ ፣ ጥቃት የጀመረው
መቅደስን አቃጥሎ ፣ ካህን የመተረው
አራት ኪሎ ገብቶ ፣ በደም የሰከረው
ጥፋቱ ሳይሰፋ ፣ በጊዜ እንቅበረው ።

የመናፍቅ ፓስተር ፣ የአምልኮ ከንቱ
የእርግማን ፍሬ ፣ ዲያቢሎስ አባቱ
በዚህ ፀረ ማርያም ፣ ሸንጋይ ባንደበቱ
ከሚኒሊክ ግቢ ፣ ከቤተ መንግሥቱ
ትእዛዝ እየወጣ ፣ ተለኩሶ እሳቱ
ኦርቶዶክስ ይፈጃል ፣ ይቀላል አንገቱ
ወንጌል ያስተማረን ፣ ሲፈፀም ትንቢቱ
ምስክሮች ሆንን ፣ ደረሰ ሰዓቱ ።

ፅዋው እስኪሞላ ፣ የፈጣሪ ጌታ
ቤተ ክህነትን ፣ አማኝ ሊያንገላታ
ምዕመን ሊሰቃይ ፣ እረፍት ሊያጣ ፋታ
የዚህ እርኩስ መንፈስ ፣ ክንዱ ሊበረታ
የቀደመ ትንቢት ፣ ነውና ግዴታ
መጨረሻው ደርሶ ፣ የማታ የማታ
በሥላሴ መቅሰፍት ፣ በትር እስኪመታ
ተግተን እንለምን ፣ በፀሎት እንበርታ ።

ታዛቢው

January 23, 2020